የWisconsin Medicaid አባላት

# የጤና ጥቅማጥቅሞችዎን ይያዙ (Keep Your Health Benefits)

(Wisconsin Medicaid Members **Keep Your Health Benefits**)

የWisconsin የጤና እንክብካቤ ጥቅማ ጥቅሞችን (እንደ BadgerCare Plus, Medicaid, ወይም MAPP) ካገኙ፣ **ምዝገባዎን በዓመት አንድ ጊዜ ማደስ አለቦት።**

## በማደሳሻው ጊዜ ምን እንደሚጠበቅ

1 ከእድሳት ወርዎ ሁለት ሳምንታት በፊት ፓኬት እንልክልዎታለን። ለምሳሌ፣ እድሳትዎ በጥቅምት ወር ከሆነ፣ በመስከረም ወር አጋማሽ ላይ ማሳወቂያ እንልክልዎታለን። በሸፋኑ ላይ ሊፈጠር የሚለውን ክፍተት ለማስቀረት ፓኬትዎን እንዳገኙ ያድሱ።

2 በፋይሉ ላይ ያሉንን መረጃዎች ማደስ ሊጠበቅብዎት ይችላል። ይህም የቤተሰቡ ዝርዝርዎች፣ ገቢ፣ እና እንሱራንስን ሊያካትት ይችላል። መጨረሻ ላይ ማረጋገጭ እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ።

3 የአካባቢዎ ኤጀንሲ እድሳትዎን ይገመግመዋል እንዲሁም ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጋቸው ይከታተላል። ከዝያን፣ ጥቅማጥቅሞ እየተቀየረ እንደሆነ የሚነግርዎትን ደብደቤ ይልክልዎታል።

## እድሳትዎን ማጠናቀቅ

- ለማደስ ፈጣኑ መንገድ መስመር ላይ በእርስዎ ACCESS መለያ በኩል ነው። ይግቡ ወይም መለያ በ **access.wi.gov** ላይ ያዘጋጁ።
- በፖስታ ለማደስ፣ የእድሳት ፓኬትዎን ይሙሉ እና ይመልሱ።
- በአካባቢዎ በሚገን ኤጀንሲ በኩል በስልክ ወይም በአካል በመገኘት ማሳደስ ይችላሉ። ኤጀንሲዎን በ **dhs.wi.gov/im-agency** ያግኙ።
- ለበለጠ መረጃ **dhs.wi.gov/renew** ን ይጎብኙ።

እድሳትዎን በጊዜ ማጠናቀቅ ካልቻሉ፣ ጥቅማጥቅሞችዎ ይጠናቀቃሉ። እድሳትዎን ለማጠናቀቅ ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ነፃ፣ የባለሙያ እርዳታ በ **WisCovered.com** ላይ ይገኛል። ወይም፣ የአካባቢያዊ አንቀሳቃሽ ለማግኘት ወደ **211** ይደውሉ።

P-10049AM (06/2024)

# የእድሳት ጥያቄዎች እና መልሶች

## እድሳት ምንድን ነው?

ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ማመልከቻ ሲያስገቡ፣ እንደ ቤተሰብዎ፣ ገቢዎ እና ኢንሹራንስዎ ያሉ ነገሮች ለክልሉ በዝርዝር ሰጥተዋል። ጥቅማጥቅሞችዎን ማስጠበቅ መቻል አለመቻልዎን ለማየት፣ መረጃውን በየዓመቱ ማዘመን ይጠበቅብዎታል። ይህ ሂደት ማሳደስ ይባላል።

## መቼ ነው የማሳድሰው?

ለእያንዳንዱ የጥቅማጥቅም ፕሮግራሞችዎ የእድሳት ቀን ተመድቦልዎታል። ከተቻለ እነሱን ለማስተካከል እንሞክራለን፣ ግን ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ። የማለቂያ ቀናትዎን በACCESS መለያዎ ውስጥ ማግኘት ይችላሉ። **access.wi.gov** ላይ ይግቡ ወይም የMyACCESS መተግበሪያን ይጠቀሙ። መለያ ከሌልዎት ጥቅማ ጥቅሞችዎን በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ቦታ ለማስተዳደር **access.wi.gov** ላይ ይፍጠሩ።

ቃኙኝ

በስልክ ካሜራዎ

## ቀጣይ ላይ ምንድን ነው የሚፈጠረው?

ከእድሳትዎ ወር ሁለት ሳምንት ገደማ በፊት፣ ፓኬት በፖስታ እንልክልዎታለን። አሁንም ለፕሮግራምዎ ብቁ መሆንዎን ለማየት እንድንችል ምን መረጃ ማረጋገጥ ወይም ማዘመን እንዳለበት ይነግርዎታል። እንዲሁም የፓኬቱ ዲጂታል ስሪት በACCESS መለያዎ ውስጥም ይገኛል።

## ብቁ እሆናለሁ ብዬ ካላሰብኩ ለምን ማደስ አለብኝ?

እድሳትዎን እንዲያጠናቅቁ እንመክርዎታለን እና ብቁ መሆንዎን እንድንወስን እንጋብዝዎታለን። በሂደቱ ማለፍ ብዙ አዎንታዊ ምክንያቶች አሉት። ለምሳሌ፣ ልጆች ካሉዎት፣ ብቁ ባትሆኑም አሁንም ጥቅማጥቅሞችን ሊያገኙ ይችላሉ።

## በሰዓቱ ካላደስኩስ?

በአንድ አንድ ሁኔታዎች፣ ከእድሳት ወርዎ በኋላ እስከ ሶስት ወር ድረስ ዘግይቶ ማሳደስ ይችላሉ። የሚቻል ከሆነ ከአካባቢ ኤጀንሲዎ ያረጋግጡ። የማይቻል ከሆነ፣ ሌሎች ሽፋኖችን ለማግኘት እገዛ ለማግኘት ወደ **211** ይደውሉ ወይም **WisCovered.com** ን ይጎብኙ።

## ሌላ ምን ማወቅ አለብኝ?

የሕክምና እንክብካቤን አያቆዩ! አሁንም ጥቅማጥቅሞች እስካሉዎት ድረስ፣ እንክብካቤ ለማግኘት ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በ BadgerCare Plus፣ ክትባቶችን፣ የሕክምና ምርመራዎችን እና የሐኪም ማዘዣዎችን ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላሉ።